# ከ"ብዙ-ዐየሁ" ደራሲ ለአቶ(?) ጋምቢ መልስ

አቶ ጋምቢ ያልፃፍኩትን ጽፎና አንብቦ ከሶኛል። በመፅሃፉ ውስጥ እንዳስቀመጥኩት፤ እነ ታደሰ "ኢሕአፓን" በ"ብራችን" ላይ እስከማፃፍ ደርሰዋል ተብሎ ያልተጻፈ በሚያነቡ ሰዎች የተከሰስኩበት አይነት መሆኑ ነው።

እኔ የፖለቲካ ታጋይ ወይም አታጋይ አልነበርኩም። በቡድን ተፋላሚ ወይም አፋላሚ አልነበርኩም። ስለተካሄዱት የግድያ ወንጀሎች የቀባሪ አርጂ ለመሆን አልተነሳሁም። በችሎታ ወይም በራስ መተማመን ማነስ መንጠልጠያ ፈላጊ አልነበርኩም።

የድርጅትና የገንዘብ አስተዳደር ባለሙያ ነበርኩ። አቅሜን ሳልቆጥብ አገሬን ለማገልገል የተዘጋጀሁ ነበርኩ። ሁኔታው የፈቀደውን ያህል አስተዋፅኦ አድርጌአለሁ። አቶ ጋምቢ ይሄን እንደወንጀል ቆጥሮብኛል።ፍርዱን ለሚያውቁኝና ለአንባቢያን እተወዋለሁ። የዓለም ባንክ ያቀረበልኝን ወፍራም ደሞዝና ጥቅማ-ጥቅም ለምኔ ብዬ አገሬ የቀረሁት አገሬን ስለማስቀድም ነው። ከአምስቱ አህጉራት ከቀረቡ ከ3ሺ 2መቶ በላይ ተወዳዳሪዎች ብቸኛው አፍሪቃዊ ሆኜ በዓለም ባንክ መመረጤ የስራ ችሎታ ስላለኝ ነው። ደርግም ከአገር እንዳልወጣ የወሰነው ጠቃሚነቴን ገምቶ ነው። በመሆኑም ደርግ ፈላጊዬ ነበር እንጂ እኔ ደርግን ፈላጊ አልነበርኩም። በየጊዜው የተሾምኩት አቶ ጋምቢ በአግቦ እንዳለው የመንግስቱ ሰላይ ወይም አገልጋይ ስለነበርኩ አልነበረም። አስተዋፅኦዬ ይፈለግ ስለነበረ ነው።

እኔን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን አገር ለቀው ቢወጡ፣ ወይም በወህኒ ለመታጎር ቢመርጡ፣ ወይም መንግስትን ላለማገልገል አድማ ቢመቱ ብሎም ወታደሮች የሲቪሉን ቦታ ሁሉ ቢሸፍኑ ኑሮ የኢትዮጵያ ዕድል የተሻለ ይሆን ነበር ብሎ አቶ ጋምቢ ያምናል። ይህ የተሳሳተና መስመር የሳተ እምነት ነው። በደርግ ዘመን በቅንነት ያገለገልን ሰዎች የህዝቡን ተስፋ የታለመውን ያህል ባናለመልምም በይበልጥ ሊደርስበት ይችል ከነበረው ስቃይ ከለላ ሆነንላታል።

ይልቁን፤ አሁን ስለወደፊቱ በጥሞና እንመካከር፤ ላለፈ ክረምት ቤት የሰራ የለምና። ቢሆንም፣ ከስህተቱ ወይም ከታሪክ የማይማር ህዝብ ከመከራ

አዘቅት አይወጣም። መጽሃፉን ለመጻፍ ያነሳሳኝ አንድም ይህ ግንዛቤ ነው። “ምን አደከመህ? ትርፉ ከሰዎች ጋር መቀያየም ነው” ያሉኝን ችላ ብዬ የሆነውን በመተረኬ አቶ ጋምቢ በስልጣን የባለጉ ሰዎችን አጋለጥክ ብሎ ተቆጣኝ። በሌላ በኩል ለምን አሳጥረህ ጻፍክ ብሎ ወረፈኝ። ፍርዱን ለአንባቢ ትቼዋለሁ።